www.fag.gov.et

ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ በመ/ቁ 05393 ጎዳር 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሠጠው ትዕዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43087 በታህሳሥ 11 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. ያደረጉት ስምምነት ሕግና ሞራልን የማይቃረን በመሆኑ በእርቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277 የተመዘገበ በመሆኑ የተጀመረው አፈፃፀም ተቋርጦ በዕርቁ መሠረት እንዲፈጸም ታዟል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐሩት መለሰ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የአቶ ብሩ ቆርቾ ወራሽ ብርቅነሽ ብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ክፍሌ ሐብደታ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00808 ጳጉሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26283 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪው አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ቁጥሩ 292 የሆነውን ቤት ብር 4500 /አራት ሺ አምስት መቶ ብር/ የሸጡልኝ ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ጉዳዩ ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ባደረጉት ዕርቅና ግልግል ያለቀ ስለሆነ ቤቱን ያስረክቡኝ የሚለው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ አመልካች ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተስማሙት መሠረት የተቀበሉትን የቤቱን ዋጋ ብር 760 /ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እና የገደብ መቀጫ ብር 2000 /ሁለት ሺ ብር/ ለተጠሪ አሟልተው ያልከፈሉ ስለሆነ በቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

www.fag.gov.et

የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በይግባኝ የሚያስቀርብ ነጥብ የለውም በማለት ዘግቶታል። አመልካች ይኸ ውሣኔ ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረግነውን ስምምነት ወደ ጐን በመተው የተወሰነ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪው በበኩል አመልካቹ በዕርቁ ውል መሰረት ያልፈፀመ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረነዋል። መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪው ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም የግልግል ውል ያደረጉ መሆኑ አልተካደም። አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የግልግል ስምምነት አመልካች ከተጠሪው የተቀበለውን ብር 760 /ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እና የቤት ሽያጭ ውሉ በመቅረቱ መቀጫ ብር 2000 /ሁለት ሺ ብር/ ሲከፍል ተጠሪው ደግሞ አመልካች ቤቱን ያስረክበኝ የሚለውን ክስ ለመተው የተስማሙ መሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል።

ይህ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የተደረገው የግልግል ስምምነት በመጀመሪያ የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል የማስቀረት ውጤት እንደሚኖረው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3308 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል። ይህም በመሆኑ ተጠሪው እና አመልካች ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉት የግልግል ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3312 ድንጋጌዎች መሠረት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር በመሆኑ ይኸው በግልግል ውላቸው ላይ የተስማሙበት ጉዳይ ማለትም አመልካች በስምምነታቸው መሠረት ብር 2760 / ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እንዲከፍል ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን ሸጦልኛልና ያስረክበኝ በማለት በግልግል ውል ቀሪ የሆነውን ጉዳይ የማንቀሣቀስ እና የመጠየቅ መብት የላቸውም። ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን ለተጠሪው እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል።

ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00808 ጳግሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26283 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል ይፃፍ።
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።

ይህ ፍርድ ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ